መስከረም 0 8 2012
4-0/0117/12

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጉምሩክ ኮሚሽን
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Customs Commission No.1

ለጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች በሙሉ
<u>በያሉበት</u>

ጉዳዩ፡- <u>መመሪያ ቁጥር 160/2012 ለአፈፃጸም መላክን ይመለከታል፡፡</u>

የገቢዎች ሚኒስቴር በቁጥር 1/51/12 መስከረም 05 ቀን 2012 ዓ.ም በፃፈው ደብዳቤ የጉምሩክ ቀሪ ቀረጥና ታክስ መክፈያ ጊዜ ለመወሰን የወጣውን መመሪያ ቁጥር 160/2012 አያይዞ የላከልን ሲሆን ፤በመመሪያው መሰረት እንዲፈፀም አሳስቦናል፡፡

ስለሆነም የጉምሩክ ቀሪ ቀረጥና ታክስ መክፈያ ጊዜ ለመወሰን የወጣውን መመሪያ ቁጥር 160/2012 10 ገፅ ከዚህ ደብዳቤ ጋር ተያይዞ የተላከ ሲሆን፤በመመሪያው መሰረት በጥብቅ ዲሲፕሊን እንዲፈፀም እናሳውቃለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ወንድወሰን ደገፋ ካሣ
የጉምሩክ ኮሚሽን የጽ/ቤት ኃላፊ

<u>ግልባጭ፤</u>
- ለጉምሩክ ኦፕሬሽን ዘርፍ
- ለህግ ተገዥነት ዘርፍ
- ለተቋማዊ አቅምና ድጋፍ ዘርፍ

<u>ጉምሩክ ኮሚሽን</u>

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የገቢዎች ሚኒስቴር
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF REVENUES

ቀን መስከረም 0 5 2012
Date
ቁጥር ፕ/51/12
Ref.No

**ለጉምሩክ ኮሚሽን**
**<u>አዲስ አበባ</u>**

**ጉዳዩ፡- <u>መመሪያ ስለመላክ</u>**

የጉምሩክ ቀሪ ቀረጥና ታክስ መክፈያ ጊዜ ለመወሰን የወጣውን መመሪያ ቁጥር 160/2012 ከዚህ ጋር በማያያዝ የላክንላችሁ ስለሆነ በመመሪያው መሠረት እንዲፈፀም አሳስባለሁ፡፡

ከሰላምታ ጋር

አዳነች አበቤ
ሚኒስትር

**<u>ግልባጭ፣</u>**

- ለሕግ ተገዥነት ዘርፍ
  <u>ገቢዎች ሚኒስቴር</u>

**Phone:** +251 11 662 98 00/ 01/02/03/04/05/06/07/08 **Fax:** /+251 11 662 98 17
**face book page:** ministry of revenues. **FBP:** mor Ethiopia **Twitter:** erca@twitt
**web site:** http//www:erca.gov.et **P.o. Box:** 2559 Addis Ababa, Ethiopia

የበለፀገች
ኢትዮጵያ!

# የጉምሩክ ቀሪ ቀረጥና ታክስ መክፈያ ጊዜ ለመወሰን የወጣ መመሪያ

## ቁጥር 160/2012

የገቢዎች ሚኒስቴር

መስከረም 2012 ዓ.ም

## የጉምሩክ ቀሪ ቀረጥና ታክስ መክፈያ ጊዜ ለመወሰን

## የወጣ መመሪያ ቁጥር 160 /2012

አስመጪዎች የሚፈለግባቸውን ቀሪ የቀረጥና ታክስ ዕዳ በአንድ ጊዜ መክፈል በማይችሉበት ወቅትየዕዳ መክፈያ ጊዜ መፍቀድ አስፈላጊበመሆኑ፤

የገቢዎች ሚኒስቴር በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 182(2)መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

### ምዕራፍ አንድ

### ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "ቀሪ የጉምሩክቀረጥና ታክስ መክፈያ ጊዜ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 160/2012" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ፤

1/ **"ባለዕዳ"** ማለት ዕቃ ከተለቀቀ በኂላ ያልተከፈለ ቀረጥና ታክስ የተገኘበት ላኪ ወይም አስመጪ ነው፡፡

2/ **"ቀሪ ቀረጥና ታክስ"**ዕቃ ከተለቀቀ በኂላ የሚወሰን የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነው፡፡

3/ **"አስተዳደራዊ ቅጣት"**ማለት የጉምሩክ ህግና ደንብ በመተላለፍ ወይም ግዴታን ባለመፈጸም በአስመጪው ወይም በላኪው ላይ የሚጣል አስተዳደራዊ መቀጮ ነው፡፡

4/ **"የውሳኔ ማስታወቂያ"** ማለት ክፍያ እንዲፈጸም ኮሚሽኑ ለባለዕዳው የሚሰጠውየፅሑፍ ማስታወቂያ ነው፡፡

5/ **"ዕዳ"** ማለት ለኮሚሽኑ በወቅቱ መከፈል ሲገባው ያልተከፈለ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ሲሆን ፤ወለድና መቀጫንም ይጨምራል፡፡

6/ **"የቀሪ ቀረጥና ታክስ ወለድ"** ማለት ሳይከፈል በቀረው የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ላይ በጉምሩክ አዋጅ 859/2006 አንቀጽ 122 (2) መሠረት የሚወሰን 10 በመቶ ወለድ ነው፡፡

7/ **"ቅድመ ክፍያ"** ማለት ያልተከፈለ ቀሪ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስየለመክፈል የክፍያ ጊዜ ሲፈቀድ ባለዕዳው የክፍያ ጊዜ ስምምነት ከመፈረሙ ከአጠቃላይ ዕዳው ውስጥ አስቅድሞ በመቶኛየሚከፍለው የገንዘብ መጠን ነው፡

8/ **"ንብረት"** ማለት የባለዕዳው የሚንቀሳቀስወይም የማይንቀሳቀስ ሀብት ሲሆን በባንክ የተቀመጠ ገንዘብንና የከበሩ ማዕድናትንእንዲሁም ግዙፋዊ ህለወት የሌላቸውን ሀብቶች ይጨምራል፡፡

9/ **"ቀሪ ክፍያ"** ማለት ባለዕዳው ያልተከፈለ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ለመክፈል ከኮሚሽኑ ጋር በሚገባው የክፍያ ጊዜ ስምምነት መሠረትቅድሚያ ክፍያ ከተከፈለ በኋላ የሚቀረው ዕዳ ሲሆን ወለድና መቀጫንም ይጨምራል፡፡

10/**"የቀሪ ክፍያ ጊዜ ስምምነት"** ማለት ባለዕዳው ወለድና መቀጫን ጨምሮ የተጠየቀውን ቀሪ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ በአንድ ጊዜ መክፈል ባለመቻሉ ኮሚሽኑ ተጨማሪ የዕዳ መክፈያ ጊዜ የሚፈቅድበት ስምምነት ነው፡፡

11/ **"ሐራጅ/ጨረታ"** ማለት ወለድና መቀጫን ጨምሮ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ባለመከፈሉ ምክንያት የባለዕዳው ሀብት ተይዞ የሚሸጥበት ሥርዓት ነው፡፡

12/ **"አዋጅ"** ማለት የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2011 (እንደተሻሻለ)ነው፡፡

13/በዚህ መመሪያ ትርጉም ያልተሰጣቸው ቃላት በአዋጁ የተሰጣቸውን ትርጓሜ ይይዛሉ፡፡

3. **<u>የመመሪያው ተፈፃሚነት ወሰን</u>**

**ይህ መመሪያ፡-**

(ሀ) ዕቃ ከተለቀቀ በኋላ ወለድና መቀጫን ጨምሮ ቀሪ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ በተወሰነበት አስመጪ ወይም ላኪ ላይ ፣እና

(ለ) ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልባቸው ወደ አገር ውስጥ የገቡ ዕቃዎችን ከታለመላቸው ዓላማ ውጪ ጥቅም ላይ ባዋለ ወይም አለአግባብ በተገለገለ አስመጪ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

## ስለድህረ-ዕቃ አወጣጥ ኦዲትየቀሪ ቀረጥና ታክስ አሰባሰብ

### 4. የውሳኔ ማስታወቂያ ስለመስጠት

1/ የሚመለከተው የሥራ ክፍል ዕቃ ከተለቀቀ በኋላ ቀሪ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስና ወይም መቀጫና ወለድ ለተወሰነበት ባለዕዳ የውሳኔ ማስታወቂያበጽሑፍ ይሰጣል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የቀሪ ቀረጥና ታክስ የውሳኔ ማስታወቂያ ለባለዕዳው በአግባቡ ሊደርሰው ይገባል፡፡

3/ በዚህአንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) መሠረት ለባለዕዳው የተላከው የውሳኔ ማስታወቂያ በአግባቡ ደርሶታል የሚባለው፡-

(ሀ) ባለዕዳው ወይም ህጋዊ ወኪሉ የውሳኔ ማስታወቂያውን ፈርሞ ሲረከብ፣

(ለ) ባለዕደውወኪሉ ያልተገኘ እንደሆነ የውሳኔ ማስታወቂያው በድርጅቱ ጽ/ቤት ወይም በግለሰቡ መኖሪያ ቤት አግባብነት ባለውና በግልጽ በሚታይ ቦታ ላይ ሲለጠፍ ነው፡፡

4/ ባለዕዳው የተጠየቀውን ቀሪየጉምሩክ ቀረጥና ታክስዕዳ ክፍሎ እስከሚያጠናቅቅ ድረስ ባልተከፈለው ቀረጥና ታክስ ላይ ወለድ ይታሰባል፡፡

5/ በውሳኔ ማስታወቂያው ላይ ቅሬታ ያለው ባለዕዳ በጉምሩክ አዋጅ ላይ በተደነገገው መሠረት ቅሬታውን የማቅረብ መብት ይኖረዋል፡፡

5. **ንብረት ስለመያዝ**

1/ የውሳኔ ማስታወቂያ የደረሰው ባለዕዳ በ30 (ሰላሳ) ቀን ውስጥ ዕዳውንበተረዘመ ጊዜ ለመክፈል ስምምነት መግባት አለበት፡፡

2/ ባለዕዳው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ዕዳውን ያልከፈለወይም ለመክፈል ስምምነት ያልገባ እንደሆነ ንብረቱ ተይዞ በጫረታ ይሸጣል፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የተያዘ ንብረት እስኪሸጥ ድረስ ለዚህ ተግባር ተብሎ ወደ ተቋቋመው የተያዙ ንብረቶች ማቆያ /ማከማቻ/ ቦታ ተወስዶ ጥበቃ እየተደረገለት ይቆያል፡፡

4/በዕዳ የተያዘው ንብረትከተያዘበት ከአስር የስራ ቀናት በኂላ በጨረታ መሸጥ ይኖርበታል፡፡

5/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 ድንጋጌ ቢኖርም ንብረቱ የሚበላሽ ከሆነ የንብረቱን ባህሪ ከግምት ውስጥ በማስገባት የተያዘውን ንብረት ኮሚሽኑ ወዲያዉ ሊሸጠው ይችላል፡፤

6/ በዚህ አንቀጽ መሠረት የባለዕዳው ንብረት ተሸጦ ለዕዳ ማካካሻ ከዋለ በኂላ የተረፈ ገንዘብ ካለ ለባለዕደው ተመላሽ ይደረጋል፡፡

7/ የዚህ መመሪያ አንቀጽ 11(5) እና 12 የተመከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ባለዕዳው በዚህ መመሪያ መሠረት የዕዳ መክፈያ ስምምነት ከገባ በኂላ በስምምነቱ መሠረት ክፍያውን ያልፈጸመ እንደሆነ ኮሚሽኑ ለባለዕዳው የአንድ ወር ጊዜ ማስጠንቀቂያ በመስጠት በዚህ ጊዜ ውስጥ ዕዳው ካልተከፈለ የዕዳ መክፈያ ስምምነቱን በማቋረጥ የባለዕዳውን የባንክ ሒሳብ ወይም ንብረቱን በመያዝ ለዕዳ ማካካሻ ሊያውለው ይችላል፡፡

## ምዕራፍ ሶስት

## ስለክፍያ ጊዜ ስምምነት

### 8.የክፍያ ጊዜ ስምምነት ስለሚፈቅድበት ሁኔታ

1/ ዕቃ ከተለቀቀ በኂላ የተወሰነ ቀሪ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ እንዲሁም አስተዳደራዊ መቀጫ በአንድ ጊዜ መክፈል ላልቻለ ባለዕዳ ኮሚሽኑ የመክፈያ ጊዜ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የዕዳ መክፈያ ጊዜ የሚሰጠው፡-

(ሀ) ባለዕዳው ዕዳውን በአንድ ጊዜ አጠቃሎ መክፈል የማይችል መሆኑ ሲረጋገጥ፤

(ለ) ባለዕዳው የመክፈያ ጊዜ እንዲሰጠው በጽሁፍ ሲያመለክት፣

(ሐ) ባለዕዳው የአጠቃላይ ዕዳውን 25 በመቶ በቅድሚያ ሲከፍል፣

(መ) ባለዕዳው ለቀሪው ዕዳ የባንክ ዋስትና ሲያቀርብ፣

3/ ባለዕዳው የተወሰነበትን ቀሪ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ዕዳ በመቃወም ወደ ክርክር የገባ እንደሆነ የዕዳ መክፈያ ጊዜ ማራዘሚያ መጠየቅ የሚችለው በቅድሚያ የተጀመረውን ክርክር አቋርጦ ዕዳውን ለመክፈል የተስማማ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንጽ (2) የተመለከቱት ቅድመ ሁኔታዎች ሲሟሉ በኮሚሽኑና በባለዕዳው መካከል የዕዳ መክፈያ ጊዜ ስምምነት የፈረማል፡፡

**9.<u>የክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ስምምነት የማይፈቀድባቸው ሁኔታዎች</u>**

1/ ከሚሽኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) በተመለከቱት ምክንያቶች የዕዳ መክፈያ ጊዜ ስምምነት ሊከለክል ይችላል፡፡

2/ ኮሚሽኑ የዕዳ መክፈያ ጊዜ የማያራዝመው፡-

(ሀ) ባለዕዳው በተሰጠው የክፍያ ጊዜ ገደብ ግዴታውን ሳይወጣ ከቀረ፣

(ለ) ባለዕዳው ተጨማሪ የዕዳ መክፈያ ጊዜ ማራዘሚያ ስምምነት የጠየቀ እንደሆነ፣

(ሐ) መቀጫና ወለድን ጨምሮ የተጠየቀው የቀረጥና ታክስዕዳ በዚህ መመሪያ ከተጠቀሰው አነስተኛ የገንዘብ መጠን በታች የሆነ እንደሆነ፣

**10.<u>ስለዕዳ አሰባሰብ</u>**

1/ የዕዳ መክፈያ ጊዜ ማራዘሚያ ስምምነት የሚፈረመው በባለዕዳው እና በቅ/ጽ/ቤቱ ሥራ አስኪያጅ ወይም እርሱ በወከለው ኃላፊ መካከል ይሆናል፡፡

2/ የገቢ አሰባሰብና ዋስትና ሂሳቦች የስራ ሂደት የተፈረመውን የክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ስምምነት በተገቢው መዝገቦ በመያዝ በስምምነቱ መሠረት በየጊዜው ሊሰበሰብ የሚገባውን ቀረጥና ታክስ እየተከታተለ በመሰብሰብ ገቢ ያደርጋል፣ መረጃውንም በማጠናቀር ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፡፡

3/ በባለዕዳውና በኮሚሽኑ መካከል የሚፈረመው የክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ስምምነት ሰነድ በሦስት ቅጂ ተዘጋጅቶ ዋናው ቅጂ ከባለዕዳው ዲክላራሲዮን ጋር መያያዝ ያለበት ሲሆን፣ሁለተኛወን ቅጂ ለባለዕዳው በመስጠት ፣ሦስተኛውን ቅጂ በገቢ አሰባሰብና ዋስትና ሒሳቦች የሥራ ሂደት ወይም ቡድን ለክትትል ይቀመጣል፡፡

4/ በክፍያ ጊዜ ስምምነቱ መሰረት ክፍያቸውን በወቅቱ በማይፈፅሙት ላይ ክትትል በማድረግ በታክስ አስተዳርአዋጁ መሠረት የባለዕዳውን ንብረት ይዞ ይሸጣል፡፡

## 11.<u>የዕዳ ክፍያ አፈጻጸም</u>

1/ በተገባው የዕዳ መክፈያ ጊዜ ማራዘሚያ ስምምነት መሠረት ባለዕዳው የቅድሚያ ክፍያውን 25 በመቶ ከከፈለ በኋላ ቀሪው ዕዳ በስምምነቱ ለዕዳ መክፈያ በተሰጠው ጊዜ ተካፍሎ በሚገኘው ውጤት መሠረት ክፍያው በየጊዜው የሚፈጸም ይሆናል፡፡

2/ ባለዕዳውየክፍያ ስምምነት ጥያቄ የቀረበው ንብረቱ ከተያዘ በኋላ ከሆነ ኮሚሽኑ ጉዳዩን ለማስፈፀም ያወጣቸውን ወጪዎች እና የቀረጥና ታክስ ዕዳውን 50%በቅድሚያ እንዲከፍል ተደርጎ ለቀሪው ዕዳስምምነት እንዲገባ ሊፈቀድለት ይችላል፡፡

3/ የክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ስምምነት የተጠየቀበት ዕዳበፍ/ቤት ወይም በፍርድ አፈፃፀም ላይ የሚገኝ ከሆነ ባለዕዳውለዕዳው የክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ለማግኘት ኮሚሽኑ የቀረጥና ታክስ አሰባሰቡን አፈፃፀም ለመከታተል ያወጣቸውን ወጪዎች በሙሉ እንደ አግባብነቱ እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ወይም /2/ የተጠቀሰውን የገንዘብ መጠን በቅድሚያ መክፈል ይኖርበታል፡፡

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ቅድሚያ ክፍያ ከተፈፀመ በኋላ በሚቀረው ዕዳ ላይ ወለድ የሚታሰበው የስምምነቱ ውል ከተፈረመበት ዕለት ጀምሮ ይሆናል፡፡

5/ ባለዕዳው በተገባው የክፍያ ጊዜ ስምምነት መሠረት በየወሩ መክፈል ያለበትን ዕዳ ሳይከፍል የቀረ እንደሆነ እና በቀጣዩ የክፍያ ጊዜ ያልተከፈለውን ጨምሮ ለመክፈል ጥያቄ ያቀረበ እንደሆነ ኮሚሽኑ ውሉ ሳይቋረጥ እስከሚቀጥለው የክፍያ ጊዜ ድረስ ጊዜ ሊሰጠው ይችላል፡፡

12. <u>የዕዳ መክፈያ ጊዜ ገደብ</u>

1/በዚህ መመሪያ መሠረት ለባለዕዳው የሚሰጠው የዕዳ መክፈያ ጊዜ ከዚህ በታች የተመለከተው ይሆናል፡፡

(ሀ) ከብር 100,000እስከ ብር500,000ለሆነዕዳ አራት ወር፣

(ለ) ከብር 500,001 እስከ ብር 1,500,000 ለሆነ ዕዳ ሰባት ወር፣

(ሐ) ከብር 1,500,001እስከብር 3,000,000 ለሆነ ዕዳአሥር ወር፣

(መ) ከብር 3,000,001እስከ ብር 10,000,000 ለሆነ ዕዳ አንድ ዓመት ከስድስት ወር፣

(ሠ) ከብር 10,000,000 በላይ ለሆነ ዕዳሁለት ዓመት ፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው የዕዳ መጠን በትይዩ ለተመለከተው የክፍያ ወር ተካፍሎ የሚገኘው ዕዳ በየወሩ የሚከፈል ይሆናል፡፡

## <u>ምዕራፍ አራት</u>

## <u>ልዩ ሁኔታዎች</u>

13.<u>ልዩ ሁኔታ</u>

1/ በዚህ መመሪያ መሠረትለባለዕዳው የተሰጠው የዕዳ መክፈያ ጊዜ ከዕዳው መጠን አንጻር እየታየ ተጨማሪ የዕዳ መክፈያ ጊዜ የሚያስፈልገው መሆኑ ከታመነበት ኮሚሽነሩእንደሁኔታው ተጨማሪ የዕዳ መክፈያ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚሰጠው ተጨማሪ የዕዳ መክፈያ ጊዜ በማንኛውም ሁኔታ ከአምስት ዓመት መብለጥ የለበትም፡፡

2/በዕዳ መክፈያ ጊዜ ስምምነቱ መሠረት ክፍያ የሚፈፀምበት ቀን የስራ ቀን ካልሆነ ክፍያው በቀጣዩ የስራ ቀን መፈፀም አለበት፡፡

3/ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ሲባል ጳጉሜ የነሀሴ ወር አካል ሆኖ ይቆጠራል፡፡

## ምዕራፍ አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 14. የተሻሩና ተፈፃሚነት የሌላቸው መመሪያዎች

1/ የጉምሩክ ቀሪ ቀረጥና ታክስ ዕዳ መክፈያ ጊዜ ስምምነት መመሪያ ቁጥር 69/2004 በዚህ መመሪያ ተሸሯል፡፡

2/ ይህን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም አሠራር በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

### 15. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

1/ይህ መመሪያ ከመፈረሙ በፊት ተጀምረው ውሳኔ ያላገኙ ጉዳዮች በቀድሞው መመሪያ መሠረት ውሳኔ ያገኛሉ፡፡

2/የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም ይህ መመሪያ ከመውጣቱ ባፊት የቀሪ ቀረጥና ታክስ ዕዳ ውሳኔ የደረሰው ባለዕዳ በነባሩ መመሪያ መሠረት የዕዳ ክፍያ ስምምነት አለመግባቱ የተረጋገጠ እንደሆነ በዚህ መመሪያ መሠረት የዕዳ መክፈያ ጊዜ ስምምነት እንዲገባ ሊፈቀድለት ይችላል፡፡

### 16. መመሪያው የሚፀናበት ቀን

ይህ መመሪያ በገቢዎች ሚኒስቴርሚኒስትር ተፈርሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ-መስከረም 05-ቀን 2012ዓ.ም

አዳነች አበቤ

የገቢዎች ሚኒስቴር ሚኒስትር